# መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት አስከባሪ ነው

# ወይስ ለህዝብ ፍርድ የሚፈለግ ወንጀለኛ ?

ከጌታቸው ጋረደው

መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ባለው ከፍተኛ ጥላቻ የትግራይን ህዝብ ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ሬፐብሊክ ለማወጅ ወደበረሀ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ችግር ቢጋጥመውም ተስፋውን ባለመቁረጥ ስለታገለ፣ ሳያስበው ለአስራ አምስት አመታት ገዛ። የሱ ዋናው ችግር፣ የሚጠላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን የሱ የትግል ተባባሪዎች ስለነበሩ እነሱን በማባረር በመግደል በማሰር ስለአስወገዳቸው ዛሬ ብቸኛው የኢትዮጵያ ገዥ ለመሆን ችሏል። የመጀመሪያውን አስራ ሶስት አመታት ሊገዛ የቻለው እንደሁኔታው አመጣጥ ዘዴውን እየቀያየረ ቢሆንም፣ በመጨረሻ የሚጠቀምበት ዘዴ ስለአጣ የሚያደርገው ቢጨንቀው ብሄራዊ የፖለቲካ ምርጫ ለማድረግ ፈቀደ፡ ይህንን የፈቀደው ባላገሩንና ገበሬውን በጥቅም ስለገዛ ምርጫውን እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ነበር ፡ ግን እነደአሰበው ሳይሆን ከምርጫው በፊት በአጭር ጊዜ ተደራጅተው ህዝቡን ለምርጫ ያዘጋጁት ቅንጅት ለአንድነትና ለደሞግራሲ ድርጅቶች ከጠበቁት በላይ ከፍተኛ ድምጽ ስለአገኙ፣ መላ የኢትዮጵያ ህዝብ ጤነኛ አየር ለመተንፈስ ቻለ፣ ግን በመለስ ዜናዊ የማጭበርበርና የውሸት ዘዴ ይህ ደስታ ወደሀዘን ስለተለወጠ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ መንግስታት ድጋፍ ከእጁ ሊወጣ የነበረው ስልጣን ስለተመለሰለት፣ የምርጫው አሸናፊዎች የቅንጅት መሪዎች በሀሰት ውንጀላ ወደ እስር ቤት ሲገቡ የሀሰት ምስክሮች እያቃራበ በቀጠሮ ሲያጉላላቸው ከቆየ በኋላ ስለአልተሳካለት፣ የመጨረሻው ውሳኔ ለየካቲት ወር ተቀጥሯል። ይህንን የፍርድ ቤት ውሳኔ የኢትዮጵያ ህዝብ በከፍተኛ ጉጉት ሲጠባበቅ የታሰሩት መሪዎቻችንም ወደሚናፍቁት ቤተሰቦቻቸው ለመመለስ ቀናት ሲቆጥሩ፣ ሳይታሰብ የመለስ ጦርነት ሱማሊያ ስለተጀመረ መላው ህዝብ ሀሳቡን ወደጦርነቱ ስለአዞረ፣ በእስር ቤት የሚሰቃዩት መሪዎቻችን ተረሱ፣ ስለእነሱ ምንም የሚነገር ነገር ስለጠፋ የሚያስታውሳቸው በመጥፋቱ በጣም ያሳዝናል። ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዲመጡ በተጠየቁ ጊዜ ቃላቸውን ሰጥተው ወዲያው የሚመለሱ መስሏቸው ነበር፣ከታሰሩ አመት ሲያልፋቸው እኛም የኢትዮጵያ ህዝብ እስከእስር ቤቱ ደጃፍ ሸኝተን ከተመለስን በኋላ ከንፈራችንን ከመምጠጥና ወይ ጉድ ከማለት አልፈን ያደረግንላቸው ጠቃሚ እርምጃ ስለሌለ እጅግ ማፈር ይገባናል።

ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል እንደሚባለው ምሳሌ መለስ ዜናዊ ገንዘብ በጣም ስለሚወድ በቃኝን ሰለማያውቅ የሱማሌ ጦርነት ለእሱ ታላቅ ረዴኤት ስለሆነ ጦርነቱን በፍጥነት ጀምሮ ጉዳዩ የማይመለከተውን የኢትዮጵያን ወታደር ወደ ጦር ሜዳ ልኮ ያስፈጀዋል። የሱማሌ ህዝብ ለአስራ አምስት አመታት መንግስት አልባ ሆኖ ሲኖር አሁን ባለፉት ወራቶች ህዝቡ ተሰብስቦ በሸሪያ የሚመራ መንግስት አቋቁሞ በመጠናከር ላይ ሳለ፣ መለስ ይህንን መንግስት በመቃወም ሱማሊያ ሽብረተኞች የሚፈለፈሉበት አገር ስለሆነች መጥፋት ይገባታል በማለት ከአሜሪካ መንግስት ጋር ዶልቶ ሰላማዊውን ህዝብ እየፈጀ ይገኛል። ሱማሌዎች በተፈጥሮ በጣም ችኩል ስለሆኑ በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ የመለስ መንግስት ወታደሮቹን በአንድ ሳምንት ውስጥ ከሱማሊያ ካላስወጣ፣ ጀሀድ አውጀን ከፍተኛ ጉዳት ይደርስበታል በማለት ስለአሰፈራሩ፣ መለስ የአሜሪካንን በቀል ለመበቀል ከአሜሪካ በቂ መሳሪያና ገንዘብ ስለአገኘ፣ ምንሊክ ቤተመንግስት ተቀምጦ ተኩስ መጀመር አግባብ አይደለም፣ መለስ ለተኩሱ መጀመር የሰጠው ምክንያት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር ሳይቀደሙኝ መቅደም ይገባኛል ይላል፣ መለስ ሱማሊያ ያላትን ዝግጅትና ሀይል ምን ያህል እንደሆነ ከአሜሪካኖች በሚያገኘው መረጃ ስለአገኘ ሱማሊያ እንደምትጎዳ ስለምታውቅ ከመለስ በፊት አትተኩስም ነበር፣ ሱማሊያ ሀይል ቢኖራት ኖሮ በሶስት ቀን ውስጥ መላ ትጥቋ አልቆ ባልተሸነፈች ነበር። መለስ ይህንን ጦርነት የጀመረው የአሜሪካንን ትእዛዝ ለመፈጸም፣ በዚህ አሳቦ ለጥቂት ጊዜያት ስልጣን ላይ ለመቆየት ነው።

መለስ ችግሩን ለማስወገድ ሰላማዊ መንገድ ሳይፈልግ ጦርነቱን በመጀመሩ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሌላውን አገር በመውረር በታሪኳ ተመዘገበች። ከመለስ በፊት የነበሩትን የኢትዮጵያን መሪዎች ብንመለከት፣ ወራሪ ቢመጣባቸውም ጉዳዩን አጥንተው ችግሩን ለመፍታት ሰላማዊ መንገድ ፈልገው ካቃታቸው፣ ወራሪ ወሰን ጥሶ ከገባ፣ አገርንና የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ አጸፋውን ያስከፍሉታል። ለምሳሌ የጣሊያን መንግስት በወጫሌው ስምምነት አንቀጽ 17 በፈለገው መንገድ ተርጉሞ ሲያቀርበው፣ ኢትዮጵያ ለማናቸውም የውጭ የፓለቲካ ስራ በጣሊያን መንግስት በኩል መስራት ይገባታል ስላለ፣ አጼ ምንሊክ ነጻዋን አገር ለጠላት አስረክቤ ልመና የሚሄድበት ምክንያት ስለሌለ ይህ አንቀጽ መለወጥና መሻሻል፣ ሲገባው፣ ይህ ተቀባይነት ካላገኘ፣ ስምምነቱ በሙሉ መሰረዝ አለበት በማለት በጉዳዩ ላይ በሰፊው ለመወያየት አጼ ምንሊክ በራስ መኮንን የሚመራ ልኡካን ወደ ሮማ ልከው ስለአልተሳካላቸው ሰራዊታቸውን አዘጋጅተው የጣሊያንን የሰለጠነ ሀይል በመሰባበር በጣሊያን ላይ ድልን ተቀዳጁ።

በ 1928 የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት ለውጊያ ሲፈ ዝግጅት ማድረጉን የወቅቱ የአገሪቱ መሪ ንጉስ ሀይለ ስላሴ ቢያውቁም፣ እሳቸው የምንሊክን ኑዛዜ ሽረው ወይዘሮ ዘውዲቱን ንግስት ራሳቸውን አልጋ ወራሽ በማድረግ ከልጅ ኢያሱና ከአባታቸው ከንጉስ ሚካኤል ጋር ተዋግተው ቢያሸንፉም የጠላትን ዝግጅት ለመከታተል ጊዜ ስለአልነበራቸው የጣሊያን ጦር ያለብዙ ድካም መናገሻ ከተማዋን ስለያዘ፣ ንጉስ ሀይለ ስላሴ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ እንግሊዝ አገር ስለኮበለሉ ተዋጊው የኢትዮጵያ ሰራዊት ያለመሪ ስለቀረ፣ ጊዜ የፈጠራቸው ጀግኖች በደቡብ ገረሱ ዱኪ፣ በሸዋ አበበ አረጋይ በሰሜን በላይ ዘለቀ የተበታተነውን ሰራዊት አሰባስበው ውጊያ ከመጀመራቸው በፊት ችግሩን በሰላም ከጣሊያን መንግስት ጋር ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት አድርገው ስለአልተሳካላቸው የኢትዮጵያ ሰራዊት ከመናገሻ ከተማ ወጥቶ በመላ ኢትዮጵያ ተበታትኖ እንዲዋጋ ስለአደረጉ፣ በጣሊያን ዘመናዊ መሳሪያና የጭስ ጋዝ ብዙ ተዋጊ ቢሞትባቸውም በመጨረሻ አገሪቱን ከጠላት ለማዳን ችለዋል።የቀደሞዎቹ መሪዎች ጦርነትን የህዝብን እልቂት ለማስቀረት የዚህ አይነት ጥረት ሲያደርጉ፣ መለስ ዜናዊ ገንዘብ ለማግኘት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር ሳይተኩሱብኝ ተኩሻለሁ የሚለው ምክንያት ተቀባይም ይቅርታም አያገኝም።

እጅግ የሚያሳዝነው መለስ ተኩሱን መጀመሩ ብቻ ሳይሆን ይህንን ያህል እስላሞች ገድያለሁ እያለ ማሰማቱ ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የእስላምናና የክርስቲማን ሀይማኗት ያላቸው ኢትዮጵያውያን፣ በአንድነት በሰላም በመተባበር የሚኖሪባት አገር ስትሆን፣ እስላሞችን እንደጠላት እንደባዳ በመቁጠር በገደላቸው ቁጥር መፎከር እጅግ አሳዛኝ ነው። በዚህ ምክንያት ለወደፊቱ የሚደርስብን ችግር በመለስ ምክንያት ስለሆነ፣ ኢትዮጵያውያን እስላም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ይህንን ስህተት እንዲገነዘቡልን እንጠይቃለን። ነቢዩ መሀመድ እስላሞች ችግር በደረሰባቸው ጊዜ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን እስላሞችን እንዴት እንደረዱ ስላየ፣ ኢት ጵያውያን ደግ ህዝብ ስለሆኑ ከነሱ አትጣሉ በጦርም አትፈልጓቸው ስላለ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችም ለእስላሞች ከፍ ያለ ክብርና ፍቅር እንዳለን ለመግለጽ እንወዳለን።

መለስ ጦርነቱን የጀመርኩት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር ነው የሚለው ውሸት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የሱን የክህደት ስራ አያውቅም በማለት ለማታለል ነው። የመለስ አባት በፋሽሽቱ የጣሊያን ወረራ የጣሊያን መንግስት ሰላይ በመሆን የትግራይን ህዝብ ያሳስሩ ያስገድሉ ስለነበር ከነጻነት መመለስ በኋላ፣ የትግራይ ህዝብ ተሰብስቦ አቶ ዜናዊን በማውገዝ የትግራይ ህዝብ ሴት ልጁን ለአቶ ዜናዊ እንዳይድር ገዝተው ከህብረተ ሰቡ ስለአገለሏቸው፣ የመለስ አባት የሚያገቧት ሴት ስለአጡ ኤሬትሪያ ሄደው ወይዘሮ አለማሽን አግብተው መለስን ወለዱ። ወይዘሮ አለማሽ ይህንን ጉድ መለስን ከመውለድ መሀን ሆነው ቢቀሩ፣የዛሬው ችግር አይመጣብንም ነበር። የመለስ አባት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መለስን በጥላቻና በምቀኝነት ስለአሳደጉትና መለስ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጥላቻ ስላደረበት፣ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ትምህርቱን አቋርጦ በረሀ ስለገባ፣ ዛሬ የሚያደርገው

ጥፍጨፋ ገደላ እስራትና ህዝብን ማሰቃየት ከአባቱ የወረሰው የወንጀል ውርስ ነው። መለስ በግብረ አበሩ በኢሳይያስ አፈወርቂ ድጋፍ በ 1983 ኢትዮጵያን በወረረ ማግስት፤ ኤሬትሪያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ስለሆነች፤ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ነጻነቷን እንድታገኝ በማለት ለተባበሩት መንግስታት የልመና ማመልከቻ የጻፈው፤ በነጻነቱ እውጃ መለስ የቅኝ አገር መሪ በመሆን አስመራ ሄዶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ወርዶ አረቦች የሰጧቸውን ባንዲራ ሲሰቅሉ የአይን ምስክር የሆነው መለስ ዜናዊ፤ በዚህ ቀን የኢትዮጵያን ሉአላዊነትን አስከበረ ወይስ የክህደት ስራ ፈጸመባት? ከዚህ ቀን ጀምሮ ኤሬትራውያን ለሰባት አመታት ኤሬትሪያ የራሳችን ኢትዮጵያ የጋራችን በማለት የአገራችንን ሀብት የተፈጥሮ ጸጋ እየዘረፉ በውጭ አገር በመሸጥ እኛ ኢትዮጵያውያን የበላተኛ ተመልካች የሀብታም ደሀ ያደረገን መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሉአላዊነትን አስከበረ ወይስ ክህደት ሰራባት? ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን የኢትዮጵያን የመከላከያ ሰራዊት ያለአንዳች ዋስትና በመበታተን፤ ወሰናችንን ያለጠባቂ አስቀርቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ አንድ ጥይት ሳይተኩስ ግዛታችን ገብቶ ሲወረን፤ በመከላከል ፈንታ ዱብ እዳ ሆነብኝ በማለት ኢሳይያስ በሀይል የያዘውን አገር ለማስለቀቅ የወያኔ ጀሌ ወታደሮች ስለአቃታቸው፤ መለስ የበታተነውን ወታደር ሰብስቦ በማዝመት የኢትዮጵያ ወታደሮች የተያዘውን ግዛት ከማስመለስ አልፈው መለስ ለኢሳይያስ የሸለመውን የአሰብን ወደብ ለማስመለስ ሰላሳ ሰባት ኪሎ ሜትር ሲቀረው መለስ በጠቅላይ ጦር አዛዥነቱ ወታደሩ ወደፊት እንዳይሄድ ወደኋላ እንዲያፈገፍግ በማዘዝ፤ የሻቢያ ወታደሮች ከጀርባቸው እንዲተኩሱባቸው ያዘዘ፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ወታደሮቻችንን ያስገደለ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሉአላዊነትን አስከበረ ብለን እናመሰግነዋለን ወይስ በታላቅ ከሀዲነት ህዝብ ፍርድ ቤት እናቀርበዋለን? በኢትዮጵያ ወታደሮች መስዋእትነት የተመለሰው ግዛት እንዲሁም በሁለቱ አገሮች መካለል ያለው ግዛት ወሰን እንደገና በፍርድ ቤት እንዲታይ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን ማናቸውንም ውሳኔ ያለይግባኝ እቀበላለሁ በማለት መለስ ቃሉን ለፍርድ ቤቱ ስለሰጠ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ባድሜ የኤርትሪያ ግዛት ስለሆነ መለስ ውሳኔውን እንዲያከብር ስለወሰነ፤ መለስ የፈለገውን አግኝቷል።

የአንድ አገር መሪ የአገሪቱን ሉአላዊነት አስከብራለሁ ሲል አገሪቱ ያበቀለችውን ቅጠልና ዛፍ እንዲለመልም ማድረግ ብቻ ሳይሆን በአገሩቱ የሚኖረው ህዝብ ብሄራዊ ክብሩ ተጠብቆ፤ ነጻነቱና መብቱ ተከብሮለት፤ ፍትህ ሳይጓደልበት የራሱን ሳይነጠቅ፤ የሌላውን ሳይወስድ ተባብሮና ተቻችሎ በመኖር፤ የዘርና የጎሳ ልዩነት ሳይኖር ፤የአገሩቱን ሀብትና የተፈጥሮ ጸጋ በጋራ በመጠቀም፤በአገሪቱ የሚደርሰውን ችግር ተባብሮ በማስወገድ፤ገዢና ተገዥ ሳይኖር አገሪቱ ህዝብ በመረጠው ምክር ቤትና በዴሞክራሲ የተገነባ የህዝብ መንግስት ሲኖረው የአገሪቱ ሉአላዊነት ተከበረ ለማለት ይቻላል። ባለፉት አስራ አምስት አመታት የመለስ አስተዳደር ያየነው የጥቂት ዜጎችን መብትና ነጻነት የሚያስከብር የጎሰኛ መንግስት አስተዳደር ስለሆነ በማህበራዊ ኑሮ በሀብታሙና በደሀው ህዝብ መካከል ያለው ልዩነት የሚያስደነግጥ ነው። በፖለቲካ በኩል ህዝቡ ዴሞክራሲ የሰጠውን መብቱን ተጠቅሞ ምርጫያ ቢያደርግ መለስ በማጭበርበር ዋሽቶ አሸንፌያለሁ በማለት ስልጣኑን ለብቻው ይዞ የተመረጡትን አባላት አስሮ በክህደት ወንጀል ሲከሳቸው፤ የአገር ሉአላዊነት ተከበረ በሚባልበት አገር አንድ መቶ ዘጠና ሶስት ሰላማዊ ዜጎች በጥይት ደብድቦ የገደለ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አስከበረ ማለት እጅግ አሳፋሪ ነው።

መለስ ዜናዊ ለገንዘብና ለስልጣን የአሜሪካ ቅጥረኛ ሰራተኛ ስለሆነ አሁን በሱ ማሊያ የሚያደርገውን ጭፍጨፋና ገደላ የአውሮፓ መንግስታትም ድምጻቸውን ሳያሰሙ ስለደገፉት የእንግሊዝ ጋዜጦች our darling ብለው ጽፈውለታል፤ የዚህ አይነት ወንጀል በኢትዮጵያና በጎረቤት አገሮች ላይ የሚሰራ ከመለስ ሌላ ማንም ስለማይገኝ፤ በኢትዮጵያ ሆነ በአለም ብቸኛው ከሀዲና ወንጀለኛ መለስ ዜናዊ ነው። መለስ ዜናዊ የሳዳም ሁሴንን አሟሟት ከተመለከተ ባለሳምንት እሱ ነው። ከሁሉም የሚያሳዝነውና አሳፋሪው ነገር የኢትዮጵያ ህዝብ ለአስራ አምስት አመታት በመለስ እጅ ሲሰቃይ ሲገደል ሲራብ ሲዋረድ የኢትዮጵያ ወታደር በመቃወም ፈንታ

የመለስ መሳሪያ ወገኑን ልጁን ገዳይ ሆኖ የኖረው ሳያንሰው፤ አሁን ለመለስ ጥቅም በማያገባው በማይመለከተው ጉዳይ ሱማሊያ ዘምቶ ሰላማዊ ጎረቤቱን እየገደለ እሱም ይሞታል። ወኔ ካለው ለመብት ተቆርቋሪ ከሆነ የቤት ውስጥ ጠላቱን መለስንና ግብረ አበሮቹን ገሎ መሞት አይሻልም? ለአገርና ለወገን ደምን አፍስሶ ህይወትን ሰውቶ ብህራዊ ግዳጅን መፈጸም ይሻላል ወይስ ለመለስ ጥቅምና ስልጣን ሰው አገር ሄዶ የውሻ ሞት መሞት? ጀግናው በላይ ዘለቀ ከመቃብሩ ቀና ብሎ የኢትዮጵያን ወታደር ቢመለከት እንዴት ባፈረ እንዴት ባለቀሰ።

የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ነው? ከላይ እንደተጠቀሰው የሱማሊያ ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ሁሉም ያተኮረው በዚሁ ላይ ስለሆነ፤ በእስር ላይ የሚገኙትን መሪዎቻችንን ከመርሳታችን ሌላ ባለፉት ሶስት ወራቶች ብዙም እንቅስቃሴ አላደረግንም፤ ምክንያቱም አቶ አንዳርጋቸው ጽጌና አቶ ብርሀነ መዋ የሚባሉ የፖለቲካ ጠበብት የቅንጅትን ስም ለውጠው ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር Kinijit international leadership የሚባል ስም ስለአወጡ ተደናግጠን ስንቀመጥ፤ እነሱም ስደተኛውን ከፋፍለው ስለያዙት ጎራችንን ለማወቅ ስለአልቻልን በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ እንደግፈው የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለድሞክራሲ የት እንደደረሰ አናውቅም። የቅንጅት እውነተኛው ተወካዮች እኛ ነን ቢሉም እነሱም ሆኑ ሌሎች ለተወካይነታቸው ተጨባጭ ማስረጃ አላቀረቡም፤ ከዚህ ሌላ አንዱ ሌላውን በመወንጀል ስለሚነታረኩ ይህንን አሳፋሪ መነካከስ መስማት ስለአልፈለግን በርቀት መመልከት ተገደናል። ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የሚለው ስም መላ የኢትዮጵያ ህዝብ የተቀበለው በአለምም የታወቀ ስለሆነ ስሙን መለወጥ ለምን አስፈለገ? በአሰራር በኩል ያለው ልዩነት ምንድነው? አገር ቤት ያለው ቅንጅት ምን እንደሚሰራ ለማወቅ የደጋፊነት መብት ስላለን እንደንጉሱ መንግስት የማናውቀውን ሾማችሁ ታዘዙ ማለት ትክክል አይደለም።

የትኛውን ቅንጅትን እንደሚወክል ባናውቅም አቶ አንዳርጋቸውና አቶ ብርሀነ ከሌሎች ድርጅቶ ጋር ለመስራት ቡድናቸውን ወደ ስብሰባው ልከዋል፤ ስብሰባውን አዘጋጅቶ የጋበዘው ( ኦ ኔ ግ) ሲሆን ተካፋዮች የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅት፤ የሲዳማ፤ ኡጋዴን፤ የኢትዮጵያ አርበኞች አንድ ነት ድርጅት፤ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ሲሆኑ፤ ህብረት ስብሰባው ሳይጀመር አለመካፈሉን ገለጸ። የመወያያው ሰነድ የተዘጋጀው በእንግሊዝኛ በመሆኑ ተደንቀናል፤ የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅት የአማርኛን ቋንቋ ቢጸየፍም፤ የኦሮሚኛ ቋንቀ ብሀራዊ ቋንቋችን ስለሆነ ከእንግሊዝኛ የተሻለው ኦሮሞኛው አልነበረም? ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለእዳ አይቀበለውም ይላሉ አባቶቻችን።በዚህ ስብሰባ አቶ አንዳርጋቸው የቅንጅትን ተወካዮች ወደስብሰባው በመላካቸው ግራ ተጋብተናል፤ ምክንያቱም ቅንጅት ከምስረታው ጀምሮ መሪዎቻችን እስከታሰሩ እስከአሁን ድረስ ትግላቸው በሰላማዊ መንገድ ህዝብ የመረጠውን መንግስት ለማቋቋም ስለሆነ፡ በተቃራኒ ኦኔግ ተገንጣይ ከመሆኑ ሌላ መለስ እንደሚለው ኦኔግ ተዋጊ ድሮጅት ስለሆነ ቅንጅት ተባብሮ ለመስራት ይችላል? ስለመገንጠሉ ጉዳይ የኦኔግ ተወካይ በሰጡት መልስ፤ ትግሉን ፈጽመን ሰላም ሲመጣ መገንጠሉንና አብሮ መኖሩን የሚወስነው የኦሮሞ ህዝብ ነው ይላሉ፤ አቶ አንዳርጋቸው በበኩላቸው ይህ ችግር አይደለም ለወደፊቱ በሂደት ሊለወጥ ይችላል ብለዋል። የኦሮሞ ህዝብ የወደፊት እድሉን ብቻውን ለመወሰን ከቻለ ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ የወደፊት እድል ምንድነው?በጋራ ትግል ወያኔን ካሸነፍን በኋላ የኦሮሞ ህዝብ ከኢትዮጵያ እንገነጠላለን ቢል፤ ሁለተኛ ኤሬትሪያ መፍጠር አይሆንም? መገንጠል ለኤሬትሪያ እንዳልጠቀመ ሁሉ ለኦሮሞ ህዝብም የሚያመጣለት ጠቃሚ ነገር የለም። ሀያ ሰባት የአውሮፓ አገሮች በኤኮኖሚ ትብብር በአንድነት ስለሰሩ አስደሳች ውጤት ስላመጣላቸው፤ የፖለቲካ ውህደት አድርገው የተባበሩት የአውሮፓ መንግስታት ለመመስረት ሁሉንም የሚሰበስብ ህገ መንግስት በማዘጋጀት ላይ ይገኛሉ። የአውሮፓ መንግስታት እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት በትብብሩ ወቅት ከመጀመሪያው፤ ሁሉም ያለውን እውቀት ካፒታል ጉልበት ይዞ ስለመጣ፤ ዛሬ ያሉበት ደረጃ ደረሱ፤እኛ ኢትዮጵያውያን በአንድነት እየኖርን ከችግር ከልመና አልወጣንም፤ ብንለያይ ምን ለውጥ እናመጣለን? መገንጠሉ ምንድነው የምንገነጠለው ከማነው? የጋራ ቤታችንን ለማፈራረስ ምን ህጋዊ

መብት አለን። ኢትዮጵያ በምትባለዋ አገር የምንኖር፣ አገር በቀልና ከሌላ ስፍራ የፈለስነው የተለያነን ብሄሮች፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጣንበትን ጊዜ በትክክለኛ ለመናገር ባንችልም፣ በቅደም ተከተል መጥተን የሰፈርን፣ ከሀምሳ ከመቶ ከሺህ አመታት በፊት ቢሆንም ሁላችንም አገር በቀልና ሰፋሪዎች ስልሆንን፣ ኢትዮጵያን በገንዘብ የገዛን ባለቤቶች አይደለንም።ለመሸጥ ለመለወጥ ለመበታተን ለመገንጧል ህጋዊ መብት ለንም። ኢትዮጵያ ተፈጥር ያልበደላት በቂ ጸጋና ሀብት ሲኖራት ችግራችን መልካም መሪ ማጣት ስለሆነ ይህ ሰው በመካለችን ሲገኝ፣ ማንም ይሁን ማንም ህዝብ ከመረጠው፣ ሁላችንም የምንቀበለው፣ ህገ መንግስት ካዘጋጀን ችግራችን ለማስወገድ ስለምንችል እናስብበት በግልጽ እንወያይበት። የኦሮሞ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት መሪዎች በየጊዜው እንደሚናገሩት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ በብዛት ከሁሉም የበለጠ ነው ይላሉ፣ ይህ ከሆነ የኦሮሞ ህዝብ ብዛት እያለው፣ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለ ኢትዮጵያዊው ማነው? መለስ ዜናዊ ባመጣብን የጎሳ አመራር፣የአማራና የኦሮሞ ጎሳዎች ተጋብተው ልጆች አፍርተው በሰላም ይኖሩ የነበሩት ስለተፋቱ፣ልጆቻቸውን እንደቤት እቃ ተከፋፍለው ተለያዩ። የኦሮሞ ህዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት ከኢሳይያስ አፈወርቂ የሚያገኘው እርዳታ ለራሱ ጥቅም እንጂ ለኦሮሞ ህዝብ በማሰብ አይደለም፣ ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት እንደማይፈለፈል ሁሉ ከኢሳይያስ አፈወርቂ ለኦሮሞ ህዝብ ማርና ወተት አይፈስለትም። የሻቢያው መሪ መለስን ለማስፈራት የኦኔግን ታጋዮች ለጊዜው ቢያቀርባቸውም፡ የሚፈልገው ሲሞላለት እንደሚያገላቸው የታወቀ ነው። የኦሮሞና የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት መለስ ዜናዊ ስለሆነ በህብረት ብንታጋል በአጭር ጊዜ ችግራችንን ለማስወገድ ስለምንችል፣የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅት መሪዎች፣ተከፋፍለን ለመኖር እንደማንችል ተገንዝበው ቢጋራ እንድንሰራ እንጠይቃቸዋለን።እስከዛሬ ላንስማማ ስለተስማማን መለስ ለያይቶ ተጠወመብን።ህብረቱ ስለማይከፋ እንሞክረው

ይህንን ጽሁፍ ከመደምደማችን በፊት ስለ አቶ አንዳርጋቸውና ስለ አቶ ብርሀነ በጥቂቱ እንነጋገር። የሱማሊያ ጦርነርት ከተጀመረ በኋላ መለስ ደጋግሞ እንደተናገረው፣ ጠላቶቻችን ሻቢያ፣ ኦኔግና ቅንጅት ናቸው ስላለ፣ መለስ የቅንጅት መሪዎችን ለመፍታት ስለማይፈልግ የነአንዳርጋቸውንና የኦኔግን ስብሰባ፣ እንደወንጀል በመቁጠር በሚቀጥለው ቀጠሮ ለወራትና ለአመታት ለማሰር ስለሚፈልግ ይህንን ካደረገ ለዚህ በህግም በታሪክም ተጠያቂዎች ብርሀነና አንዳርጋቸው መሆናቸውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያወቀው ያስፈልጋል፣ ምክንያቱም ሁለቱ ሰዎች ከቅንጅት ተወክለን የመጣን ነን በማለት ከኦኔግ ጋር ስለተሰበሰቡ፣ የታሰሩት መሪዎቻችን ስለዚህ ጉዳይ ምንም እንደማያውቁ ማንንም ወክለው እንዳልሆነ ለፍርድ ቤቱ መግለጽ ያስፈልጋቸዋል።

አቶ አንዳርጋቸውና አቶ ብርሀነ ከአገራችው ወጥተው ወደ አሜሪካና አውሮፓ ከመምጣታቸው በፊት አቶ ብርሀነ የነጋዴዎች ምክር ቤት ፕርዜዳንት፣ አቶ አንዳርጋቸው በከፍተኛ አመራር የወያኔ መንግስት ሰራተኛ ስለነበሩ የኑሮ ችግር አልነበረባቸውም።ሁለቱም ወያኔ ያወጣውን ህገ መንግስት ተቀብለው የኤሬትሪያን መገንጠል ደግፈው ታማኝነታቸውን ያስመሰከሩ ሱሉሁኑ አገር ቤት ቢቆዩ ምንም የሚደርስባቸው ችግር አልነበረም። ወደዚህ መጥተው የተጠናከረውን የስደተኞች ትግል ለምን ከፋፈሉት? ፍላጎታቸው ምንድነው? ከታጋዩ ጋር ለመታገል ስለፈለጉ፣ ስደተኛው ማን መሆናቸውን ስለአወቀ ፊት ስለነሳቸው፣ በአዲስ አስተሳሰብ የቅንጅትን ስም ለውጠው ለመስራት ቢፈልጉም አልተሳካላቸውም።ትልቁ ችግራቸው ስደተኛው ተሰልፎ የሚጮህ ብቻ ስለሚመስላቸው ማናቸውንም ነገር እነሱን አስፈቅዶ እንዲሰራ ይፈልጋሉ፣ እነሱ ቢንቁቸውእንጂ በቂ ችሎታ ያላቸው ዜጎች አሉ። ሁለቱ እራሳቸውን የፓለቲካ ጠበብት አድርገው የሚያዩ ስለሆነ ያለፉትን አመታት አገር ቤት በማባከናቸው ስለሚቆጩ፣ በመጨረሻ ደቂቃ የድል አጥቢያ አርበኛ በመሆን በድል አድራጊነት ታጅበው ለመመለስ ስለሚፈልጉ ትልቁ በሽታቸው ይህ ነው። ሹመት ያዳብር እንላቸዋለን። የቃሊቲው ቅንጅት መንፈስ ነው መንፈስ አየይሞትም አይለወጥም አይሻርም። ይህንን ጠላትም ወዳጅም ይወቀው። አምሌክ ኢትዮጵያን ይጠብቃት አሜን። ፍራንክፉርት፣ ጥር 7-1999 (15..01.2007 )